# ጥሩ ፍርድን ማሳደግ እና ሌሎችን አለመፍረድ

ካህን ግሬጎሪ ኤ ሽዋርትዝ
የሰባዎቹ ቡድን አባል

ብዙ ነገሮች አስቸጋሪ የሆኑ ፍርዶችን ማድረግ እንዳለብን በሚያደርግ አለም ውስጥ እንኖራለን። ነገር ግን አዳኝ ሌሎችን “አትፍረዱ” የሚል ትእዛዝ ሰጠን።1 ይህን እንዴት ማድረግ እና በማታለል እና በእርኩሳት በተሞላው አለም ውስጥ ጥሩ ፍርድ ማድረግ እንችላለን። ጓደኞችን በመምረጥ፣ ዘለአለማዊ ጓደኛን በማግኘት፣ ወይም ቤተሰባችንን እንድንረዳ እና ጌታን እንድናገለግል ስራን በመምረጥ አይነት በጣም አስፈላጊ የሆኑትን ውሳኔዎች ስናደርግ በደንብ መፍረድ አለብን። ምንም እንኳን አዳኝ ሌሎችን እንዳንፈር ቢጠይቀንም፣ ጥሩ የሆነ ፍርድ እንድናደርግ ይጠብቅብናል።

ብዙ ጊዜ ከሰዎች ጋር ያለንን ጓደኝነት የሚቀይር ወይም ሌላ ትርጉም እንድንሰጥ የሚያስደርግ ፈጣን ውሳኔ ስለሰዎች እንድናደርግ ተገፍተን እራሳችንን እናገኛለን። ብዙ ጊዜም ትንሽ መረጃ ስለነበረን ወይም በፊት ለፊታችን ካለው አሳልፈን ሳንመለከት ፈጣን ፍርድ እናደርጋለን።

በምሳሌ በማሳየት፣ ከወንድማቸው ከአልዓዛር ጋር በቤተኒ ውስጥ የሚኖሩትን የማርያም እና የማርታን ቤት ኢየሱስ ስለጎበኘበት ጊዜ ታሪክ ይናገሩ ነበር። ለመምህሩም ይህ በጻድቃዊ ቤት እረፍት እና ደስታን የሚያገኝበት አስደሳች ቦታ ነበር። በሚጎበኝበት አንድ ቀን ማርታ ምግብን ለማዘጋጀት ትሯሯጥ ነበር እና ማርያም በመምህሩ እግር በታች ተቀምጣም ለመማር መረተች።

“ማርታ ግን አገልግሎት ስለ በዛባት ባከነች፤ ቀርባም። ጌታ ሆይ፥ እኔ እንድሠራ እኅቴ ብቻዬን ስትተወኝ አይገድህምን? እንኪያስ እንድታግዘኝ ንገራት አለችው።

“ኢየሱስም መልሶ። ማርታ፥ ማርታ፥ በብዙ ነገር ትጨነቂአለሽ ትታወኪማለሽ፥

“የሚያስፈልገው ግን ጥቂት ወይም አንድ ነገር ነው፤ ማርያምም መልካም ዕድልን መርጣለች ከእርስዋም አይወሰድባትም አላት።”2

ማርታን በእምነቷ በበታችነት የሚያሳያት ብዙ የሰንበት ክፍል ትምህርቶች ስለዚህ ታሪክ ተዘጋጅተው ነበር። ነገር ግን ስለዚህች ታላቅ ሴት ማርታ እውቀት እና ምስክር ዝልቅ የሆነ አስተያየት የሚሰጠን ሌላም ታሪክ ነበር። ይህም የሆነው አዳኝ ወድሟን አልዓዛርን ከሞት ለማስነሳት በመጣበት ጊዜ ነበር። እርሱ እንደሚመጣ ወዲያው እንደሰማችም ኢየሱስን ለማግኘት የሄደችው ማርታ ነበረች። ከእርሱም ጋር እንደተገናኘችም “አሁንም ከእግዚአብሔር የምትለምነውን ሁሉ እግዚአብሔር እንዲሰጥህ አውቃለሁ አለችው።”

ክርስቶስም የትንሳኤን ታላቅ ትምህርት ከእርሷ ጋር ተካፈለ።

“ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፤ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል፤

"ሕያው የሆነም የሚያምንብኝም ሁሉ ለዘላለም አይሞትም፤ ይህን ታምኚያለሽን?"

እርሷም እንዲህ በማለት በሀይለኛ እና ልብ በሚነካ ምስክር መለሰች፤ "አዎን ጌታ ሆይ፤ አንተ ወደ ዓለም የሚመጣው ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆንህ እኔ አምናለሁ አለችው።"3

ለስንት ጊዜ ማርታ ነገሮችን ማከናወንን ከመንፈስ ነገሮች በላይ አድርጋ እንደምታስብበት ለስንት ጊዜ ተገምቶባታል? ነገር ግን በወንድሟ ሞት ጊዜ ፈተናዋ ላይ የነበራት ምስክር የእውቀቷን እና ዬምነቷን ዝልቅነት አሳይቷል።

ብዙ እህቶች የመጀመሪያውን ታሪክ ሰምተው እንደማሪያም ወይም እንደ ማርታ አይነት እንደሆኑ ያስቡ ነበር፣ ነገር ግን እውነት የሚገኘው ሰውን በሙሉ በማወቅ እና ጥሩ ፍርድን በመጠቀም ነው። ስለማርታ ብዙ በማወቅ እርሷ ዝልቅ የሆነ መንፈሳዊ ጸባይ ያላት፣ ስለአዳኝ ሚስዮን እና በህይወት ላይ ስላለው መለኮታዊ ሀይልደፋር ምስክር ያላት እንደሆነች እናውቃለን። ስለማርታ ያለን ግምት የዚህች ሴትን እውነተኛ ጸባይ እንዳናውቅ አድርጎናል።

በአስተሳሰቤ እንደወጣት ዶክተር፣ ፈጣን ፍርድ ስለመፍረድ ታላቅ ትምህርት ተምሬአለሁ።፡በለሊት ድንገተኛ አደጋ የደረሰባቸው በሚጠገኑበት ክፍል ውስጥ እየሰራሁ እያለሁ አንድ ወጣት ሰውና ሚስቱ በጣም እያመማት ስለነበር መጡ። በአለባበሳቸው ችግረኛ ህይወት እንደነበራቸው ይታወቅ ነበር። ጸጉሩ ያልታጠበ እና ረጅም ነበር። ልብሶቻቸውም ያልታጠቡ ነበሩ እና የችግር ህይወትም በፊታቸው ላይ የተጻፉ ነበሩ።

ከመረመርኳት በኋላ ችግሩ ምን እንደሆነ እና እንዴት እንደምናክማት ነገርኩት። ይህም ሰውዬ በአይኖቹ ያለውን ፍቅር እያሳየ "ዶክተር ውዷ ባለቤቴ ደህና ትሆናለች?" ብሎ ጠየቀኝ። በዚያም ጊዜ መንፈስ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ መሰከረልኝ፣ እናም በአይኖቹም ውስጥ የአዳኝን ምልክት አየሁ። ይህም ሰው ለሌላ ያለውን ፍቅርበእውነትም አሳየ እና እኔም ያለትክክግ ፈርጄበት ነበር። ይህም ለዘለአለም የማስታውሰው ትምህርት ነበር።

ጥሩ ፍርድ ሰዎችን ለማወቅ ብቻ ሳይሆን ከሰማይ አባት ወይም ወደሰማይ አባት የሚመራን ውሳኔዎችን በምናደርግበት ጊዜ ያስፈልገናል። ስለህይወቴ አጋጣሚዎች ሳስብባቸው፣ በመጥፎ ውሳኔ ምክንያት ጌታ እንድሆን ከሚፈልገኝ ሊያዞረኝ የሚችሉ ብዙ አጋጣሚዎች እንደነበሩ አያለሁ። ወደ ትምህርት ቤት እየሄድኩኝ እያለሁ ቤተሰብ እንደመጀመር፣ በወንጌሉ በሙሉ ተሳታፊ እንደመሆን፣ ገዘብ በሚያጥርበት ጊዜ አስራትን እና በኩራትን እንደመስጠት፣ እና በሚያስቸግር ጊዜ ጥሪን እንደመቀበል አይነት ውሳኔዎች ስለመስዋዕት በተጨማሪ እንድማር ረድተውኛል። በህይወት ውስጥ መንፈሳዊ ውሳኔ በሆኑት ላይ የአለም ፍድርን በማድረግ በህይወት ብዙ በረከቶች አምልጠዋል።

ጥሩ ፍርድ ያሳደጉ ሰዎች ብዙ ጸባያት አሉ። አስፈላጊ የሆኑ ውሳኔዎችን ለመድረስ የሚያስችሉ እንደዚህ አይነት ፍርዶችን ለማሳደግ አራት መመሪያዎችን ላቀርብላችሁ እፈልጋለሁ።

አንደኛ፣ የግል መለኪያችሁን ከኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ጋር የተደረደረ አድርጉ። ሰው ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ሳይመልከት ጥሩ ዳኛ መሆን አይችልም።ወንጌሉ ሰዎችን ወደ ደስታ የመምራት ችሎታ አለው። አንዳንድ የአለም አሳቦች የሰው ዘር መለኪያውን እራሱ እንዲያዘጋጅ በማድረግ እንዲምታቱ ያደርጋሉ። በዚህም ምክንያት፣ "አዲስ ነምግባር" የሚባል ነገሮችን እንሰማለን። ይህ አባባል የሚያታልል ነው። የስነምግባር መሰረት ዘለአለማዊና የማይቀየሩ ናቸው፣ ወይም አዲስ ትርጉም ለእነሱ መፈለግ አይገባንም። ለወጣቶች እነዚህ መሰረቶች በ"For the Strength of Youth" ፅሁፍ ላይ ተፅፈዋል። እነዚህ መሰረቶች ከኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ጋር የሚስማሙ ናቸው እና በጎልማሳ ህይወትም መቀጠል የሚያስፈልጋቸው ናቸው። እኛ ጎልማሳዎችም እነዚህን ፅሁፎች ማጥናት እና መጠቀማችን ጥሩ ሳይሆን አይቀርም።

ሁለተኛ፣ የህያው ነቢይ መልእክትን አዳምጡ። የነቢዩን ምክሮች ብናዳምጥ ኖሮ ምን አይነት የገንዘብ ችግርን ለማምለጥ እንችል ነበር? ወሲብ ነገሮችን የሚያሳዩ ሙቪዎችን ለማስወገድ ጥሩ ውሳኔን በማድረግ ስንት ጋብቻዎች እና የልብ ስበራን ለማዳን ይቻል ነበር? እያንዳንዱ የአጠቃላይ ጉባኤ እና *Ensign* ገጼት ከተጠቀምንባቸው ወደ ጥሩ ፍርድ የሚመሩን የነብያትን ምክር የያዙ ናቸው። ችላ ስንላቸው ግን ምንም ምክንያት የለንም።

ሶስተኛ፣ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የማዳመጥ ግንኙነትን አሳድጉ። ከተጠመቅን በኋላ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ተሰጥቶናል፣ ነገር ግን በህይወታችን አስፈላጊ ፍርዶች ላይ እንደሚረዳን እንረሳለን።በዚህ ህይወት አስቸጋሪ ውሳኔዎች እንደሚመጡብን ስላወቀ ነው ጌታ ይህን ስጦታ የሰጠን። ጥሩ ፍርድን ለማሳደግ ይህን ድምፅ ማዳመጥ አስፈላጊ ነው። የማዳመጥ ግንኙነትን ለማሳደግ የሚቻለው ትንሽ የዝምታ ድምፅን ለማዳመጥ እና ለማሰላሰል በሚቻልበት በጸጥተኛ ቦታ ነው። ይህም ጸጥተኛ ቦታ ውስጣዊ እና በውጪም የሚገኝ ነው። ስለዚህ፣ የምናዳምጠውን ሙዚቃ ማቆም ብቻ ሳይሆን በነፍስ ውስጣዊ የሆነውን የኀጥያትን ጩኸት በማቆም ነው። ይህም በጣም የሚያስፈልገውን መንፈሳዊ ግንኙነት ይከፍታል።

ክርስቶስ "ሰላምን እተውላችኋለሁ፥ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ፤ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጥ አይደለም። ልባችሁ አይታወክ አይፍራም" ብሏል። መንፈስ ቅዱስን በማዳመጥየሚመጣው ሰላም በህይወት ውስጥ መጥፎ ውሳኔ የማድረግን ፍርሀት ያጠፋል።

አራተኛ፣ ትእዛዛትን ጠብቁ። የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የመጠበቅ ፈቃደኝነት ብዙ ቃል የተገቡ በረከቶችን እንድናገኝ ያደርጉልናል። መፅሐፈ ሞርሞን የኢየሱስ ክርስቶስ ሌላ ምስክር ከመሆኑ ሌላ ትእዛዛትን የመጠበቅ እና ያለመጠበቅ ውጤታዎችን የያዘ ነው። ጌታ ለኔፊ እንዳለው፣ "እና ትዕዛዛቴን እስከጠበቅህ ድረስ ትበለፅጋለህ…።"5

ይህ አይነት ቃል ኪዳንም በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ በነበሩት ነብያት በሙሉ ተደጋግሟል። እነዚህ ቃላቶች እውነት እንደሆኑ የሚመሰክሩ የአንድ ሺህ አመቶች ታሪኮች ተፅፈዋል። ጥሩ ፍርድን በምናሳድግበት ጊዜም እነዚህ መልእክቶች እኛን ይረዳሉ። ጥሩ ፍርድን በደንብ የምንለማመደው እና የምንማረው ጌታ በሚሰጠን ትእዛዛት ውስጥ ነው

በህይወታችን አስቸጋሪ ውሳኔዎች በምናደርግበት ጊዜ ጻድቃዊ ፍርድን በሚመለከት ያሉትን መሰረቶች እና መመሪያዎች እንድንከተል እና ጌታ ከእኛ ጋር እንደሆነ የማወቅ ሰላም እንዲኖረን ጸሎቴ ነው። ከግል አጋጣሚዬ እነዚህ መመሪያ መሰረቶች እውነት እንደሆኑ የምመሰክረው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው፣ አሜን።